# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፦** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ሚያዚያ 1 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**የወያኔ እቅድ ተቃውሞና ትችት እየቀረበበት ነው፤**

**የአባይ ግድብ ስራ ምሁራኖችን ያገለለ በመሆኑ እውን የመሆኑ ጉዳይ ያጠራጥራል ተባለ፤**

የወያኔው ቡድን ሰሞኑን በጀመረው በአባይ ወንዝ ላይ ግድብ መስራት በሚል አዲስ የቅስቀሳ ዘመቻ ትችት እና ታቃውሞ እየቀረበበት መሆኑ ታወቀ::ድንገት ሳይታሰብ ሰሞኑን ይፋ የተደረገው በአባይ ወንዝ ላይ ግድብ መስራት የሚለው የወያኔ ማሳሳቻ ፕሮፓጋንዳ የስልጣን እድሜ ለማራዘሚያነት እና ግዜ ለመግዣነት የታቀደ ባዶ ቅስቀሳ እንደሆነ እየተገለፀም ይገኛል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ቅዳሜ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ሳይታሰብና ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ ታላቁ የሚሊኒየም ግድብ ፕሮጀክት በሚል የመሰረት ድንጋይ መጣሉን ተከትሎ በምሁራኖች እና በባለሙያዎች ከፍተኛ ትችት እና ተቃውሞ እየቀረበበት እንደሚገኝ ታወቀ::

በአሁኑ ግዜ መላው የሀገሪቱ ህዝቦች የእለት ጉርስ መቅመስ ተስኖዋቸው በየቤታቸው ጾማቸውን ውለው እያደሩ ባለበት ሰዓት የወያኔ ቡድን ከውስጥ ከራሱ ነባር እና አዳዲስ ካድሬዎች በሚነሳ ጥያቄና ከውጭ በአፍሪካ በተፈጠረው የፖለቲካ ግለት በመደናገጡ የተነሳ በአባይ ላይ ግድብ ለመስራት ተነስቻለሁ የሚል ፕሮፓጋንዳ መጀመሩ ምሁራኖች እየተቃወሙት እና እየተቹት እንደሚገኝ ታውቆዋል::

ስልጣን ላይ ከተቀመጠ 20 ዓመታትን ያስቆጠረው መለስ ዜናዊ ከውስጥ የራሴ ናቸው ከሚላቸው የተለጣፊ ቡድን ካድሬዎች በየግዜው ተደጋጋሚና አስቸጋሪ ጥያቄዎች እየተነሱበት በመቸገሩና በአሁኑ ሰዓት ደግሞ በሰሜን አፍሪካና በአረብ ሀገራት የተከሰተው የህዝብ አመጽ ስላስፈራው

የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ ያለ ምንም ቅድመ ዝግጅት እና ያለ በቂ ጥናት ድንገት በአባይ ላይ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ስራ ጀመርኩ ብሎ የመሰረተ ድንጋይ ማኖሩን ተከትሎ ባለሙያዎች እየተቃወሙ መሆኑ ታውቆዋል::

ወያኔ የአምስት ዓመቱን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የልማትና የኢኮኖሚ ሰነዶች በሚል አውጥቶ የበተነ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ አንዱንም ተግባር ላይ ያላዋለ መሆኑ በገሀድ እየታየ ባለበት በዚህ ወቅት የአባይን ግድብ በድንገት ስራ ላይ አውላለሁ ብሎ መነሳቱ እጅግ ከባድ እና ውስብስብ ነው ሲሉም ምሁራኖች ይተቻሉ::

የአምስት ዓመት የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በሚል በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የባቡር መስመር ለመዘርጋት ከ7 ቢሊዮን ብር በላይ ሊያወጣ እቅድ መያዙ.....የሀገር አቁዋራጭ የባቡር መስመር ለመዘርጋት ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚያስፈልገው እያወቀ...... የአስፓልት መንገድ ግንባታ ፕሮግራሞችን መያዙ እየተገለፀ ..... የግልገል ግቤ ቁጥር 3 እና ግልገል ግቤ ቁጥር 4 የመብራት ኃይል ማመንጫ ከ68 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚያስፈልገው እየታወቀ እና አንዱንም ተግባር ላይ ባላዋለበት በዚህ ግዜ የአባይን ግድብ ለመስራት ያልታሰበ እና ዱብ እዳ መፍጠሩ ሊታመን የማይችል በቅርቡም ተግባራዊ ሊሆን የማይችል እቅድ ሲሉ እነዚሁ ምሁራኖች እና ኢኮኖሚስቶች ይናገራሉ::

በቅርቡ ስራ ጀመረ የተባለው የጣና በለስ የመብራት ኃይል ማመንጫ እንኩዋን ገና ስራው ያልተጠናቀቀ ከመሆኑም በላይ ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ እንደሚያስፈልገው የገለፁት የኢኮኖሚ ባለሙያዎች የታቀዱትን ተግባር ላይ አውሎ መስራት ሳይቻል እንደገና ሌላ ከባድ ፕሮጀክት መንደፉ በህዝብ ላይ ጫና ከመፍጠሩም በላይ ለኑሮ ውድነት አይነተኛ ሚና እንደሚጫወት ገልፀዋል::

የአውሮፓ የኢንቨስትመንት ባንክ ...የአፍሪካ ልማት ባንክ .....የቻይናና የህንድ ባንኮች በብድርና በእርዳታ በሰጡት ገንዘብ ያቀደውን ስራ ተግባር ላይ ያላዋለው የወያኔ ቡድን ያለ አንዳች መነሻ ገንዘብ በባዶ እጁ በጨበጣ አባይን እገድባለሁ ብሎ መነሳቱ በፊት ከነበረው በላይ በህዝቡ ኑሮ ላይ ጫና እንደሚፈጥር የገለፁት የኢኮኖሚ በለሙያዎቹ ሀሳቡ በጎ ቢሆንም ግዜው ይቀረዋል ሲሉም አክለው ይመክራሉ::

መንገድ እሰራለሁ.....ፋብሪካ እገነባለሁ......ባቡር መስመር እዘረጋለሁ...... እያለ ከዓለም ባንክ ...ከአውሮፓ ህብረት....ከቻይናና ከህንድ ባንኮች.... ከአሜሪካ መንግስት እና ከሌሎችም ሀገራት መንግስታት ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በብድር እና በእርዳታ የሰበሰበ ቢሆንም በዚህ ገንዘብ ቃል ከገባቸው ውስጥ አንዱንም ተግባራዊ ሳያደርግ እንደገና አሁንም ለፖለቲካ ፍጆታና ለእድሜ ማራዘሚያ ሲባል ብቻ ያውም ከህዝብ በሚዋጣ 80 ቢሊዮን ብር ግድብ እገነባለሁ ብሎ ቡራ ከረዩ ማለቱ አስገራሚ ጉዳይ ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል::

አክለውም ይህንን ያህል ግዙፍ ግድብ ከባለሙያዎች እውቅና ውጭ እገነባለሁ ብሎ በጥቂት ቀናት ውስጥ በምስጢር ታቅዶ ለህዝቡ ድንገት ይፋ መደረጉ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ያሉት

ባለሙያዎቹ ስራው እንደማይሰራና ብዙም እንደማይገፋበት የወያኔ ባለስልጣናት ቢያውቁም ሆን ብለው ይህችን የውጥረት ግዜ ሊያስተነፍሱበት የመረጡት ስልት መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

ያለ ብድርና እርዳታ ብሎም ልገሳ በሀገሪቱ ህዝብ መዋጮ ብቻ በአጭር ግዜ የሚሰራ ተብሎ ሰፊ ቅስቀሳ እየተደረገለት ያለው የአባይ ግድብ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሱዳን ድንበር አቅራቢያ የሚገኝ መሆኑን የጠቀሱት ባለሙያዎቹ አስቀድሞ ይህንን ያህል ግዙፍ ግድብ ለመስራት ሲታቀድ ብዙ ግዜ ተወስዶ መጠናት ሲገባው የይድረስ ይድረስ እንዲያም ሲል በምን ቸገረኝነት ስሜት ተነሳስቶ የፖለቲካ ኪሳራ መሸፈኛ ለማድረግ መሞከር በሀገር እና በህዝብ ላይ መቀለድ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተው ሲገለፁ ተደምጠዋል::

80 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የሚጠይቀው ይሄው ፕሮጄክት ከሀገሪቱ የአንድ ዓመት በጀት በላይ መሆኑን የጠቀሱት ምሁራኖች ሰሞኑን በይፋ የመሰረት ድንጋይ ተጣለ ተብሎ በወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እና በባለስልጣናቱ ቅስቀሳ እየተደረገለት ቢሆንም በመጀመሪያ ስራው በአጭር ግዜ የሚሰራ ሳይሆን ግዜ ተወስዶ በጥንቃቄ የሚገነባ ከመሆኑም በተጨማሪ በባዶ እጅ ሆኖ ግንባታ ጀምሬያለሁ ማለት በህዝብና በሀገር ሀብት ከመጫወት አልፎ መቀለድ ነው ያሉት ምሁራኖቹ በአሁኑ ሰዓት ወያኔ ከደረሰበት የፖለቲካ ኪሳራና ከገባበት የፖለቲካ አጣብቂኝ ለመውጣት ሲል ይረዳኛል የሚል ስልት ነድፎ ያዘጋጀው የልጆች እቃ እቃ ጨዋታ ነው ሲሉ በምሬት ሲናገሩ ተደምጠዋል::

በአባይ ወንዝ ላይ መሰረተ ልማት መስራት ቢቻል የሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ፍላጎት ከመሆኑም በተጨማሪ በጉጉት የሚጠበቅ መሆኑን የጠቀሱት የምህንድስና ባለሙያዎች ዙሪያውን በጥልቀት ሳይታይና ባለሙያዎች ሙያዊ አስተያየተ ሳይሰጡበት ድንገት በይድረስ ይድረስ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ብቻ ለማዋል መሩዋሩዋጣቸው በእጅጉ አሳፋሪና ውድቀቱ ከባድ መሆኑን ከወዲሁ እያስገነዘቡም እንደሚገኝ ታውቆዋል::

በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ የኑሮ ውድነት ከመቼውም ግዜ በላይ ጣራ ነክቶ ህዝቡ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቆ ባለበት...... ዜጎች በአስተሳሰባቸው ብቻ እየታፈኑ ለእስር በሚዳረጉበት...... አንዱን ብሄር ከሌላው በተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶች እርስ በርስ እንዲበጣበጡ እየተደረገ ባለበት......እና ብሔራዊ እርቅ ተፈጥሮ ሁሉም ዜጎች እኩል መብት ሳይሰጣቸው ትልቅ ሀገራዊ አጀንዳ የሆነውን የአባይ ወንዝ እንደ ተራ እና ትንሽ ነገር ለፖለቲካ ፍጆታ ብቻ ለመጠቀም መሽቀዳደም ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ቆም ብሎ ሊያስብበት እና ሊያጤነው ይገባል ሲሉ ምሁራኖች አስተያየታቸውን እየገለፁ ይገኛሉ::

ከዚህ ቀደም በእቅድ ደረጃ በአፄ ኃይለ ስላሴም ሆነ በደርግ መንግስት ግዜም ቢሆን መሰል የመሰረተ ልማት ፕሮጄክቶች ተነድፎና ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የአቅም ጉዳይ ሆኖ ተግባራዊ ሳይደረጉ መቅረታቸውን የጠቀሱት እነዚሁ ምሁራኖች ደርግ ከጣሊያን መንግስት ባገኘው ሙሉ ድጋፍ በጣና በለስ ላይ ሰፊ እርሻ ልማት ለመጀመር ግዙፍ የውስጥ ለውስጥ ቱቦ ቀበራ አድርጎ የነበረ ቢሆንም ወያኔ የአራት ኪሎ ቤተ መንግስትን ሲቆጣጠር የሀገር እና የህዝብ ሀብት የሆነውን ጄኔሬተር እና የቱቦ ብረቶችን እየነቃቀለ ከጥቅም ውጭ ከማድረጉም በላይ ሌት ከቀን በመጫን ወደ ትግራይ ማሻገሩን

ያስታወሱት እነኚሁ ምሁራኖች መለስ እና ቡድኑ ዛሬ ደርሶ ሀገር ወዳድ ለመምሰል መጣራቸው አስገራሚ ነው ሲሉም ትችታቸውን ሲሰነዝሩ ተደምጠዋል፡፡

ማንም ዜጋ ሀገሩ ስታድግና ስትለማ የሚጠላ የለም ያሉት እነኚሁ ምሁራኖች የወያኔ ዘረኛ ቡድን ሀገሪቱን በክልል.....ህዝቡዋን በጎጥና በጎሳ በታትኖ ህዝቡ አንድ ልብ ሆኖ ስለ ሀገር እና ዳር ድንበር እንዳያስብና እርስ በርስ እንዳይተሳሰብ 20 ዓመታት ሲሰራ ቆይቶ ዛሬ የፖለቲካ ጨዋታው ሲያልቅበት ድንገት ያለ በቂ ጥናት ልገድብ ነው ብሎ ጨኸት ማሰማቱ ግዴለሽነቱን የሚያሳይ ነው ሲሉ ይተቻሉ፡፡

የወያኔን ፖለቲካ ያልደገፈውን ዜጋ እንደጠላት እየቆጠሩ ሲያስሩና ሲያንገላቱ አልፎ ተርፎ ተቃውሞ በወጣው ህዝብ ላይ በአልሞ ቅልብ ጦር የጅምላ ጭፍጭፋ እንዲደርስ ሲያዙና ሲያስፈጽሙ የነበሩት የወያኔ ቡድን መሪዎች ዛሬ የሀገር ልማት ግንባር ቀደም ተቆርቆዋሪና ፊታውራሪ መስለው ብቅ ማለታቸው ከዚህ ቀደም እንደተደረገው ሁሉ በመርዝ የተለወሰ ጨዋታቸውን ሊያደርጉ እንጂ ሌላ ትርጉም እንደሌለው በስፋት ህዝቡ እየተናገረ ይገኛል፡፡

ከኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም ይልቅ የሻዕቢያ ፍቅር ብሶባቸው ሀገሪቱን ወደብ አልባ አድርገው የኖሩት እነ መለስ ዜናዊ እስከ ዛሬ የሰሩትን ግፍና የፈጸሙትን አሳፋሪ ተግባር መልሰው በሀገር እና በህዝብ ላይ ለመድገም መራወጣቸው የሚጠበቅ ነው ያሉት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በአሁኑ ሰዓት በህዝቡ መሀል የተደበላለቀ ስሜት እንዲፈጠር እያደረጉ መሆኑም እየታየ ይገኛል ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ ፖለቲካ አያገባችሁም ተብለው ሲባረሩ የነበሩት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዛሬ ለወያኔ ፖለቲካ ማስፈጸሚያና የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ የሚሆን ፕሮግራም ሲታቀድ ከእናንተ ውጭ ለዚህች ሀገር ማን አለ? እየተባሉ በአሜሪካና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ቅስቀሳ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡

ለዚሁ ተግባር የሚረዳ በስድስት የወያኔ ልዑካን ቡድን ተከፋፍሎ በአሜሪካ የተለያዩ ክፍሎች በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵውያንን ለመማፀን እና ለማግባበት የተጀመረው ዘመቻ በቀጣይም ካናዳ እንግሊዝና ሌሎች ሀገሮችም እንደሚደረግ ታውቆዋል፡፡

ሊገነባ ነው የተባለው ይሄው የአባይ ግድብ ፕሮጀክት ብዙ ጥናት ያልተደረገበት ከመሆኑም በላይ በቂ ሙያዊ ድጋፍ ያልተደረገለት በመሆኑ ብዙ ስጋቶች ከወዲሁ እያሳደሩ ይገኛሉ፡፡ከሱዳን ድንበር 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ እንደሚገኝ የተነገረለት ይሄው ግድብ በከባድ የጦር መሳሪያ ቁጥጥር ስር መሆኑ እየታወቀ 80 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ እቅድ መነደፉ በቂ ጥናት እንዳልተደረገበት የሚያረጋግጥ መሆኑንም ባለሙያዎች ክፉኛ እየተቹት ይገኛሉ፡፡

በሀገሪቱ ውስጥ የተሰሩትን የመብራት ኃይል ማመንጫ ግድቦች በተለይ የግልገል ግቤ ቁጥር ሁለት በቂ ግዜ ተወስዶ ጥናት ባለመደረጉ በውሀ መተላለፊያ ቱቦው ላይ በደረሰ የመደርመስ አደጋ ከተቀመጠለት ዋጋ በተጨማሪ 27 ሚሊዮን የህዝብ ገንዘብ ሊባክን እንደቻለና አሁንም በአባይ ግድብ ላይ በቂ ጥናት ሳይደረግበት ግድቡ ተጀመረ መባሉ ለኪሳራ ሊዳርገን ይችላል የሚል ስጋት በህዝቡ ዘንድ አሳድሮዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ለሀገር እና ለህዝብ አስቦ የጀመረው እቅድ ከሆነ ሊመሰገን እና ሊበረታታ ይገባል ያሉት የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ቡድኑ አስቀድሞ በዚህ ጉዳይ ላይ ለህዝቡ መንገርና ባለሙያዎችን ሰብስቦ ሊያወያይ ሲገባው በድብቅና በምስጢር ድንገት ይፋ ማድረጉ እቅዱ ላይ ጥርጣሬ ሊፈጠር እንደቻለ ይናገራሉ፡፡የወያኔ ቡድን እውነት ከልቡ ያሰበው እቅድ ከሆነ ከህዝቡ ላይ ዘርፎ ያቋቋማቸውን ከ40 በላይ ግዙፍ የንግድ ድርጅቶችን ሸጦ ለዚህ ግድብ ማዋል ግድ ይለዋል ሲሉም ይገልፃሉ፡፡

የግድቡ ወጪ በመንግስትና በህዝብ እንደሚሸፈን የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ቢናገርም ይሄ እውን መሆኑ ያጠራጥራል የሚሉት ምሁራኖች ግድብ መስራቱ የሚደገፍ ቢሆንም 80 ቢሊዮን ብር ያህል ከተራብ እና ከተቸገረ ህዝብ ጉረሮ መንጠቅ አስቸጋሪ ነው ይላሉ፡፡በመሆኑም የወያኔው ቡድን አንድ እና ብቸኛ አማራጩ ከህዝብ ዘርፎ የጠራቀመውን ገንዘብ ለዚህ ግድብ ማዋል ግድ ይለዋል ሲሉ አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ፡፡

ሰሞኑን በተጀመረው የቦንድ ሽያጭም በተመለከተ በቂ ማብራሪያ ካለመሰጠቱም በተጨማሪ ስለ አከፋፈሉና አመላለሱ የግዜ ገደብ እንዳልተቀመጠለት ታውቆዋል፡፡ ቦንድ ማለት ለወያኔ ገንዘብ ማበደር ሲሆን መብትና ግዴታው ምን እንደሆነ አንዳችም የሰፈረ ማብራሪያ ያልተቀመጠለት በመሆኑ ወያኔ ለማጭበርበር ያደረገው ስልት ነው ሲሉም ብዙ ዜጎች እየተቹት ይገኛሉ፡፡

ብዙ የሀገሪቱ ዜጎች የግድቡን መሰራት በሙሉ ልብ ቢደግፉም በወያኔ ላይ ባላቸው ጥርጣሬ የተነሳ ገንዘባቸውን ለቦንድ ሽያጭ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆናቸው እየታየ ነው፡፡

ሰሞኑን የወያኔ ቡድን የአባይ ግድብ መሰረት መጣል ተከትሎ የመንግስት ወር ደመወዝተኛ በግዴታ የአንድ ወር ደመወዙን እንዲያዋጣ ለማስገደድ አዲስ ስልት እየተነደፈ ሲሆን ከሀገር ውጭ ያሉ ዜጎችም በግዴታ የሚለግሱበት መንገድ እየተጠናና በቅርቡም ይፋ እንደሚደረግ ይጠበቃል፡፡

ግንባታዎቹ ለሀገር እና ለህዝብ ጠቃሚ ቢሆኑም አስቀድሞ ሊሰሩ የሚገባቸው ነገሮች ባለመሰራታቸው በህዝቡ ላይ የከፋ የኑሮ ውድነት ሊያስከትል ይችላል የሚል ስጋት ያሳደረ ሲሆን ለወያኔ ግን የፖለቲካ መጠቀሚያው መሆኑ አንዳችም ጥርጥር እንደሌለው እየተነገረ ይገኛል፡፡፡